# Union of Tigreans in North America (UTNA)
## ማሕበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ (ማተሰኣ)

UTNA
P.O.BOX 73736
Washington, DC 20056
UTNA67@verizon.net

Tel. (202) 265-8702
Fax. (202) 265-8703


## እያሱ በርሀ

### ለመድረክ ተፈጥሮ በህዝባዊ ፍቅር ታጅቦ በመድረክ ያለፈ ታሪካዊ አርቲስት
### ከትግራይ ተወላጆች ማህበር በሰሜን አሜሪካ (ማ.ተ.ሰ.ኣ) የተሰጠ የሃዘን መግለጫ

እኛ በሰሜን አሜሪካ የምንገኝ የትግራይ ተወላጆች ማህበር አባላት እንዲሁም ባለንበት የዓለም አድማስ ያለነው መላው ኢትዮጵያውያን የዲያስፖራ አባላት የተወዳጁንና የዝነኛውን ምርጥ አርቲስት የእያሱ በርሄን ድንገተኛ ሞት የሰማነው በታላቅ ድንጋጤና ሃዘን ነው፡፡
አርቲስት እያሱ በርሄ ፀሃፊ፣ እውቅ ገጣሚ፣ ከያኒና የሙዚቃ ደራሲ፣ ሁሉን አቀፍ ህዝባዊ አርቲስትና ባለ ዘርፈ ብዙ ተውህቦና ተሰጠኦ፣ ይህ ቀረሽ የማይባል ሙሉእ ህዝባዊ የኪነት ሰው ነበረ፡፡
አርቲስት እያሱ በርሄ ገና በለጋ እድሜው በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ ተንሰራፍቶ የነበረውን አድሎኣዊ ስርዓት ለመታገል ትጥቅ ካነሱት የህዝብ ልጆች አንዱ በመሆን ባበረከተው ሁለንተናዊ ተሳትፎና በከፈለው ውድ መስዋእትነት የጨለማው ዘመን ተገፎ የኢትዮጵያ ህዝብ የሰላም፣ የፍትህ፣ የልማት፣ የዲሞክራሲና የእኩልነት ችቦ ቦግ ብሎ በበራበትም ዘመን የኤርትራው አምባገነናዊ ሃይል አዲሱን ስርዓት ለማጨናገፍ ያካሄደውን እኩይ ወረራ እንደ ትጥቁ ዘመን ሁሉ ሰራዊቱንና ህዝቡን በአማላይና በስርቅርቅ ድምፁ በመቀስቀስና ለተግባር በማነቃነቅ የኢትዮጵያ ህዝብ አሸናፊነት እውን እንዲሆን የበኩሉን አብይ ድርሻ ተወጥቷል፡፡
አርቲስት እያሱ በርሄ እኛ በሰሜን አሜሪካ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን በትጥቅ ትግሉ ወቅትና ከድል ማግስትም ጀምሮ ለዴሞክራሲያዊው ስርዓት ማበብ በመካከላችን በመገኘት በልዩ ልዩ መድረኮች ያበረከተውን አስተዋፅኦ በልዩ ስሜትና ትዝታ እናስታውሰዋለን፡፡
ምንም እንኳን አርቲስት እያሱ በርሄ በድንገተኛ ህልፈት በአካል ቢለየንም ባለፈ ህያው ኪነታዊ ስራው ምንጊዜም በመካከላችን እንደሚገኝ እያሰብን እሱ እስከ እለተ ሞቱ ሲታገልለት የነበረውን ፍትህ፣ ሰላም፣ እኩልነት፣ ልማትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያችን አብቦና አሽቶ እስከ ወዲያኛው ድረስ ጎልብቶ ይዘልቅ ዘንድ ያለመታከት የድርሻችንን እንደምንወጣ ቃል እየገባን አርቲስት እያሱ በርሄን በመጨረሻው ህዝባዊ መድረክ የሰነቀው ህዝባዊ ፍቅር ለዘለአለማዊው እንቅልፉ ምርኩዝ ይሁነው በማለት ለመላው ቤተሰቡ፣ ጓደኞቹ፣ ወዳጆቹና ለኢትዮጵያ ህዝብ መፅናናትን እንመኛለን፡፡

ማክሰኞ ጥር 19/2010